EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# አልኮል በመገናኛ ብዙኃን እንዳይተዋወቅ ማድረግ ለሕብረተሰብ ጤና ያለው ፋይዳ

አልኮል መጠጣት ከጥንት የአምልኮ ሥርዓቶች እስከ ዘመናዊ ማኅበራዊ ስብሰባዎች ድረስ የሰው ልጅ ባሕል አካል ሆኖ ቆይቷል። ነገር ግን፣ የአልኮል መጠጥ አላግባብ መጠቀም የሚያስከትላቸው ውጤቶች ብዙ አገራት የማስተዋወቅና ሽያጩን ቁጥጥር እንዲያደርጉ አነሳስቷቸዋል።

አልኮል መጠጣት ሱስን፣ በሽታዎችንና አደጋዎችን ጨምሮ ከብዙ የሕዝብ ጤና እና ማኅበራዊ ችግሮች ጋር የተቆራኘ ሲሆን ይህም ፖሊሲ አውጪዎች ዋነኛ ስጋት ያደርገዋል።

የምግብና የመድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011"አልኮል"ማለት ማንኛውም የአልኮል ይዘቱ ከዜሮ ነጥብ አምስት በመቶ በላይ የሆነ የመጠጥ ዓይነት ስለመሆኑ ይገልፃል። አዋጁ አስከትሎም ቁጥጥር ከሚደረግባቸውና የሰዎችን ጤና ከሚጎዱ ግብዓቶች መካከል አልኮል አንዱ መሆኑን ያስቀምጣል።

በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 18 በግልፅ ሁኔታ እንደተገለፀው ማንኛውም የአልኮል መጠጥ ከ21 ዓመት በታች ለሆኑ ሰዎች መሸጥ የተከለከለ ሲሆን የአልኮል መጠጥን በጤና ተቋም፣ በትምህርት ቤት፣ በመዋለ ሕጻናት፣ በዩኒቨርሲቲና በኮሌጅ፣ በመንግሥት ተቋማት፣ በአምልኮ ቦታ፣ በስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች፣ በሲኒማ ቤቶችና ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ መሠረት ከአልኮል ሽያጭ ነጻ እንዲሆኑ በሚወሰኑ ቦታዎች መሸጥ የለበትም።

ከገላጭ ፅሑፍ ጋር በተያያዘም በፋብሪካ ደረጃ ተዘጋጅቶ ለኅብረተሰብ የሚቀርብ ማንኛውም የአልኮል መጠጥ ገላጭ ጽሁፍ የአልኮል መጠኑን፣ በተገቢ መንገድ ካልተጠቀሙ የጤና ችግር እንደሚያመጣ እንዲሁም አልኮል መጠጣት ጽንስን ሊጎዳ እንደሚችል በጉልህ በሚታይ ጽሁፍ የሚገልጽ መሆን እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 1112/2011 ተደንግጓል።

በአሁኑ ጊዜ በመገናኛ ብዙኃን በተሞላው ዓለም፣ ማስታወቂያ ሰዎች አልኮልንና አጠቃቀሙን እንዴት እንደሚገነዘቡ ተጽዕኖ በማድረግ የተጠቃሚዎችን ባህሪ የመቅረጽ ኃይል አለው።

በመሆኑም በተለይ እንደወጣቶች እና ከመጠን በላይ የመጠጣት አዝማሚያ ያላቸውን ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ለመጠበቅ የተለያዩ አገራት የቁጥጥር አካላት የአልኮል መጠጦችን በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ለመገደብ ወይም ለማገድ ርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛሉ።

በኢትዮጵያም ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ለመጠበቅ በተለይ በአዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀፅ 60 ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው ማንኛውም የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያ እድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች ለሆኑ ሰዎች መሸጥ እንደሌለበት በማስታወቂያው ላይ በጉልህ በተጻፈ ጽሁፍ ወይም እንደአግባቡ በድምጽ መገለጽ አለበት።

በተለይ ማንኛውንም የአልኮል መጠጥ በሕዝብ መሰብሰቢያና መገልገያ ቦታ፣ በስፖርት ማዘውተሪያ፣ በአውራ ጎዳና ላይ፣ በጋራ መኖሪያ ቤቶች እና በሌሎች ቦታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት የሚጠየቅን የጤና ማስጠንቀቂያ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በማሳነስ ማስተዋወቅ ክልክል ነው።

በኢትዮጵያ ልክ እንደሌሎች ሀገራት ከአልኮል መጠጥ ጋር በተያያዘ ከፍተኛ የሕብረተሰብ ጤና ችግሮች ተደርጎ ይወሰዳል። አልኮል አላግባብ መጠቀም የጉበት በሽታዎችን፣ የልብና የደም ሥር (cardiovascular) በሽታዎችን እና ለካንሰር የመጋለጥ እድልን ጨምሮ ከተለያዩ የጤና ችግሮች ጋር የተያያዘ ነው። በኢትዮጵያ አልኮል መጠጣት ለተለያዩ አደጋ፣ ለቤት ውስጥ ጥቃት እና ለሌሎች ማኅበራዊ ጉዳዮች በተለይም ተጋላጭ በሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ የራሱን አስተዋፅኦ ያደርጋል።

መንግሥት ተላላፊ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከልና አክም ለማዳን ጥረት በሚያደርግበት ወቅት አልኮል በኅብረተሰቡ ላይ የሚያሳድረው ጫና ቀላል አይደለም። የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን እንደተቆጣጣሪ አካል፣ የአልኮል ማስታወቂያ በተለይ ለወጣቶች እና ከመጠጥ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ስጋቶችን ዝቅተኛ ግንዛቤ ባላቸው ሰዎች ላይ የአልኮል መጠጥ የሚያደርሰውን ሁለንተናዊ ችግር በመገንዘብ በአዋጅ ቁጥር 1112/2011 ስር ስለ አልኮል መጠጥ የተቀመጠውን ቁጥጥሮች ተፈፃሚ በማድረግ ላይ ይገኛል።

በዚህ አዋጅ አልኮልን ስለማስተዋወቅ ተከታዩ አንቀፅ እንዲህ ይላል « በማንኛውም የአልኮል ምርት በብሮድካስት አማካኝነት ማስተዋወቅ የተከለከለ ነው። ይህ ክልከላ ማንኛውንም የአልኮል ምርት የብራንድ ስም፣ ዓርማ፣ የንግድ ምልክት፣ የድርጅት ዓርማ፣ የንግድ መለያ ወይም ሌላ ተያያዥ መለያን የአልኮል ምርት ካልሆኑ ሌሎች ምርቶች፣ አገልግሎቶች፣ ወይም ጉዳዮች ጋር በማያያዝ ወይም በሌላ መንገድ ቁርኝት እንዳላቸው በሚያሳይ ማስታወቂያ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።» ይላል።

ከዚህ በተጨማሪም የአልኮል መጠጥን ከሎቶሪ ዕጣ ወይም ከሽልማት ጋር በማንኛውም መንገድ በማያያዝ ወይም አልኮልን በቢልቦርድ አማካኝነት የሚደረግ የማስተዋወቅ ተግባር የተከለከለ መሆኑን በዚህ አዋጅ ተገለፀ ሲሆን የአልኮል መጠጥ የሚተዋወቅበት ወይም ፕሮሞት የሚደረግበት ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ በሚመለከት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ መሠረት ተጨማሪ ገደብ ሊጣል እንደሚችል ይጠቅሳል።

በባለስልጣኑም በንቃት ክትትል የሚደረግባቸው የአልኮል ማስታወቂያዎች በወጣቶች እና ተጋላጭ ማኅበረሰቦች ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ቀላል የሚባል አይደለም። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ለአልኮል ማስታወቂያ መጋለጥ ቀደም ብሎ በወጣቶች መካከል ለመጠጣት መነሳሳትን፣ መጠጣትን መጨመርና ከመጠን በላይ የመጠጣት ሁኔታዎችን ይፈጥራል። እነዚህ አደጋዎች በተለይ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ ሕብረተሰቡ ስለ አልኮል ጉዳት ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ በሆነባቸው ውስጥ ጎልቶ ይታያል።

70 በመቶ የሚጠጋው ሕዝብ ከ30 ዓመት በታች በሆነባት ኢትዮጵያ ይህ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ እነዚህን ተጋለጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለአልኮል ማስታወቂያዎች መጋለጥን በተለይም ለወጣቶች ተደራሽ በሆኑ የሚዲያ መድረኮች እንደቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ እና ከጊዜ ወደ ጊዜ ዲጂታል ሚዲያዎች መጋለጥን ለመግታት አበክሮ በመስራት ላይ ይገኛል።

ከቁጥጥር ርምጃዎች በተጨማሪ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሰዎች አልኮል በሚዲያ ማስተዋወቅ በሕግ ስለመከልከሉ በሕብረተሰቡ ውስጥ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራዎች እየሰራ ነው። እነዚህ ሥራዎች አሉታዊ የጤና እና ማኅበራዊ ተጽኖዎችን በማጉላት፣ ኃላፊነት የተሞላበት መጠጥን በማበረታታት እና ከአልኮል ነጻ የሆኑ አማራጮችን በማስተዋወቅ የአልኮል ፍላጎትን ለመቀነስ ያለመ ነው።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482
http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/